# ትምህርት 7

## ንስሃ መግባት

መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ዓይነት ንስሃ መግባት እንዳለ ያሳያል፡፡ እነዚህም፡ -

1. ወደ ድነት (መዳን) የሚያደርስ ንስሃ፦ ይህ ንስሃ፣ ኃጢአት ማድረግ ማለት የበደሉትን ሰው ማሳዘን ብቻ ሳይሆን በዋናነት እውነተኛው ዳኛ እግዚአብሔር እያየ በደል በመፈጸም የእግዚአብሔርን ወሰን አልባ ታላቅ ማንነት እና ቃሉን መናቅ/ማዋረድ /ማቃለል መሆኑን ተረድቶ ኃጢአት በመስራቱ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ አባትነት ምን ያህል እንደበደሉ/እንደተጋፉ ተገንዝቦ እጅግ በማዘን/በመጸጸት በእግዚአብሔር ፊት በእንባ የሚቀርብ ኑዛዜና ምህረት መጠየቅ ነው፡፡ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እኛን ለማዳን የመስዋዕት በግ አድርጎ በማቅረብ የገለጠልንን ወደር የሌለው ፍቅሩ፣ ምህረቱና ቸርነቱ ሁሌ እያስደነቀን እጅግ ልንወደው፣ ልናከብረውና ልናመሰግነው ሲገባ በተቃራኒው የሚያሳዝነው ድርጊት ፈጽመን መገኘታችን በውነት ሊያሳዝነን ይገባል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ንስሃ ከእግዚብሔር ይቅርታን በማስገኘት ወደ ድነት ያደርሳል፡፡ ኃጢአት ከእግዚዚብሔር የሚለያይ/የሚያራርቅ ከበረከቱም ሁሉ የሚያጎድል ሆኖ ሳለ አምላክ ግን ከዘላለም ፍቅሩና ቸርነቱ የተሳ ይቅር እያለ ወደ ራሱ ያስጠጋን ሆኖ ሳለ መልሶ እርሱኑ የሚያሳዝንና የሚያስቆጣ ድርጊት ፈጽሞ መገኘት እንደ ዋዛ የሚታይ ሳይሆን ከልብ ሊያሳዝን የተገባ ነው፡፡ ዘሁ 15፡31፣ ዘዳ 32፡15፣ 1ሳሙ 15፡23

መዝ 51፡1-4፣ አቤቱ፥ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፤ እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ፡፡ [2] ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፥ ከኃጢአቴም አንጻኝ፤ [3] እኔ መተላለፌን አውቃለሁና፥ ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና፡፡ [4] አንተን ብቻ በደልሁ፥ በፊትህም ክፉትን አደረግሁ፥ በነገርህም ትጸድቅ ዘንድ በፍርድህም ንጹሕ ትሆን ዘንድ፡፡ (2ሳሙ 12፡7-12)

2ኛ ቆሮ 7፥10፣ "እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኀዘን ጸጸት የሌለበትን፥ ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንስሐ ያደርጋልና፤ የዓለም ኀዘን ግን ሞትን ያመጣል፡፡"

2. ወደ ድነት የማያደርስ (ለድነት የማያበቃ) ንስሃ፡ - ሰው በሰራው ኃጢአት ምክንያት የመጣበት ቅጣት ሲከብደው ወይም ይመጣብኛል ያለው ፍርድ ሲፈራና ከእጄ ይወሰዳል ያለው ክብር, በረከትና መልካም ነገር ሲያሳዝነው … የሚገባው ንስሃ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ህብረት በመበላሸቱ ማዘን ያልሆነ ንስሃ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ንስሃ ኃጢአትን መተው/መጥላት ወይም ጽቅን መውደድም ሆነ የንስሃ ፍሬ ማፍራት አያስከትልም፡፡
   ለዚህ ምሳሌ የሚሆን ንስሃ ለመጥቀስ ያህል፡ - የፈርዖን፣ የሳዖልና፣ የአስቆሮቱ ይሁዳ ንስሃ፡

## ንስሃ የመግባት ሂደት/ቅደም ተከተል

1. አንድ ሰው ንስሃ ከመገባቱ በፊት ከኃጢአት ጋር የነበረውን ንክኪ ምን እንደ ሚመስል ፈትሾ ኃጢአተኛ መሆን አለመሆኑን መለየት አለበት፡፡ ማንኛውም ሰው የሰራው ኃጢአት ከሌለ ንስሃ መግባት አያስፈልገውም ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ግን ኃጢአት የማያደርግ ማንም ሰው እንደሌለ በግልጽ ይናገራል፡፡ ነገር ግን ያደረገው /የሰራው/ ክፉ ነገር/ኃጢአት እያለ ሰው አላየኝም /አላወቀብኝም/ በማለት ንስሃ መግባት አያስፈልገኝም ማለትም ኃጢአቱ በሰው ባይታወቅ ከእግዚአብሔር ሊሰወር አይችልምና እግዚአብሔርን መዋሸት ይሆናል፡፡ የሰራው ኃጢአት መኖሩን ካወቀ ደግሞ በግልጽ አዎን እኔ ያደረግሁት ኃጢአት ያለብኝ ኃጢአተኛ ነኝ

ብሎ በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ዝቅ በማድረግ ለሰራው ኃጢአት እውቅና መስጠት እንዳለበት የእግዚአብሔር ቃል የስገነዝባል።

ኤር 14፥20፣ "እግዚአብሔር ሆይ፤ ክፋታችንን ዐውቀናልና፤ የአባቶቻችንን በደል ተረድተናልና፤ በእርግጥም በአንተ ላይ ኀጢአት ሠርተናል።"

ኤር 3፥13፣ "በአምላክሽ በእግዚአብሔር ላይ በማመፅሽ፣ ክብርሽንም ለእንግዶች አማልክት፣ በየለምለሙ ዛፍ ሥር አሳልፈሽ በመስጠት፣ ለእኔ ባለመታዘዝሽ፣ በደለኛ መሆንሽን ይህን አንድ ነገር ብቻ እመኚ" ይላል እግዚአብሔር።"

2. ባደረጉት ኃጢአት መጸጸት/ማዘን፡ - በእግዚአብሔር ስም የተጠራም ሆነ አዲስ ከእግዚአብሔር ጋር የሚተዋወቅ ሰው ኃጢአት በመስራቱ፣ የእግዝሂአብሔርን ቃል በመጣሱ ክልብ መጸጸትና ያልተገባ ስራ በመስራቱ መቆጨት አለበት። 2ቆሮ 7፡10
   እግዚአብሔር ሰውን ከአፈር አበጃጅቶ የሰራውና የሕይወት እስትንፋስ እፍ በማለት ሕያው ሰው ስላደረገው፣ እንዲህ ትንሽ የሆነውን ሰው በዘላለም ፍቅሩ የወደደው፤ ለሰው ዘር መልካም እንዲሆንለት ምድርና በውስጥዋ ያሉትን ለሰው ጠቃሚ የሆኑ ፍጥረታት እንዱሁም ጸሐይና ጨረቃን ፈጥሮ ለሰው ዘር በነጻ የሰጠ፣ ሰው በኃጢአት በወደቀ ሰዓትም ሊያድነው አንድያ ልጁን እንደ በግ በመሰዋት የኃጢአቱ ማስተሰሪያ ያደረገን አምላክ በዚህ ሁሉ ውለታው ፊንታ የሚጠላውና የሚጠየፈውን ኃጢአት በፊቱ ሰርቶ እርሱን በድሎ በእርሱም አምጾ መገኘት ከልብ መራራ ሀዘን ሊያሳዝን የተገባ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሃዘን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነና ከአምላኩ ጋር ወደ ሰመረ ሕብረትና ወደ ድነት የሚያደርስ ሃዘን ነው።
   የዓለም ሃዘን ግን ሰው የነበረውን ምድራዊ ሀብት፣ ንብረት፣ ስልጣን፣ ምቾት፣ ክብር ከማጣቱ፣ ተስፋ ያደረገው መልካም ነገር ሳይፈጸም በመቅረቱ፣ የሚከተለው ቅጣት በመፍራት …ወዘተ የሚመጣ ሃዘን ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሃዘን ወደ እውነተኛ ንስሃና ወደ ድነት ከቶ አያደርስም። ቃኤል- ዘፍ 4፡13-15፣ፈርዖን- ዘሁ 15፡31፣ ዔሳው- ዘፍ 27፡34-40፣ ከዳዊት ጋር የነበሩ ሰዎች- 1ሳሙ 30፡6፣ አኪጦፌል-17፡23፣ የአስቆሮቱ ይሁዳ - ማቴ 27፡4-5፣ ዮናስ 3፡5-10
3. ኃጢአትን መናዘዝ፡ - ያዕ 5፡16፣ አብዛኛውን ጊዜ ኃጢአት የሆነ ነገር ለማድረግ በሰው እንዳይታወቅ በመፍራት ሰው በማያይበትና በማይሰማበት ስውር ቦታ ይከናወናል። እግዚአብሔርም በደል ሲፈጸም ወዲያውኑ እርምጃ ስለማይወስድና ስለሚታገስ የማያይ ሊመስል ይችላል። ስለዚህ በሰው ፊት ሃጢአትን መናዘዝ ካለ ሰው ወደፊት በሰው እንዳይሰማበት እንዳይታወቅበት ከመፍራት ተነሳ ኃጢአት ከማድረግ ሊቆጠብ ይችላል። ኃጢአቱን በበሰለ ሰው ፊት በመናዘዙም እግዚአብሔርን ያላፈረ መሆኑን ስለሚያሳውቅበት ለወደፊቱ ለመጠንቀቅ ሊያግዘው ይችላል።
   ምሳ 28፥13 "ኀጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝና የሚተወው ግን ምሕረትን ያገኛል። ሐዋ 19፥18 "ካመኑትም ሰዎች ብዙዎቹ እየቀረቡ ክፉ ሥራቸውን በግልጥ ተናዘዙ፤"
4. ንስሃ መግባት ማለት የአስተሳሰብና የፈቃድ የአካሄድ ለውጥ ማምጣት ማለት ስለሆነ ይህን ለማድረግ ሙሉ የልብ ዝግጅት /ከልብ የሆነ ውሳኔ/ ማድረግ ይገባል። አንዴ ንስሃ ከገቡ በኂላ ቀድሞ ይወዱት የነበረው ኃጢአት መጨረሻው አሰቃቂና አስጨናቂ ጥፋት ማከማቻ መሆኑን ተገንዝቦ መጥላትና ይጠሉት የነበረውን ጽድቅ ማድረግን መለመመድ እና እግዚአብሔርን ወደ መውደድ ማዘንበል ይገባል።

5. ለፈጸሙት ኃጢአት ይቅርታ መጠየቅ፡ - ሰውን የበደሉት በደል ካለ የበደሉት ሰው ጋር ማግኘት የሚቻል ከሆነ ፈልጎ አግኝቶ ይቅርታ መጠየቅ።

እግዚአብሔርን ብቻ የበደሉበት ጉዳይ ካለ ራሱ እግዚአብሔር እግር ስር ቀርቦ ይቅርታ መጠየቅና ምህረት መቀበል ነው፡፡ በዚህ ሂደት ራስን እንዳዘጋጁ ስለ ሰው ዘር ሁሉ ኃጢአት ስርየት ራሱን መስዋዕት አድርጎ ያቀረበውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የግል አዳኝ አድርጎ በእምነት በመቀበል ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ አማካይነት እርቅና የኃጢአት ስርየት በማግኘት መኖር ነው፡፡ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሀዘን ብቻውን በጌታ ኢየሱስ ካላመኑ መዳን አያስገኝም፤ ጌታ ኢየሱስን አዳኝነት በእምነት ለመቀበል መንገድ የሚጠርግ እርምጃ ነው እንጂ፡፡

ሮሜ 2፡4-5፣ ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሓ የሚመራህ መሆኑን ሳትገነዘብ፣ የቸርነቱን፣ የቻይነቱን የትዕግሥቱን ባለጠግነት ትንቃለህ? [5] ነገር ግን በድንዳኔህና ንስሓ በማይገባ ልብህ ምክንያት ትክክለኛ ፍርዱ ሲገለጥ በእግዚአብሔር የቍጣ ቀን በራስህ ላይ ቍጣን ታከማቻለህ፡፡

6. የንስሃ ፍሬ ማፍራት፡ - በጌታ ኢየሱስ በማመን ምህረት ካገኙና የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ከሆኑ በኋላ ቀድሞ ያደርጉት የነበረውን ኃጢአት ሁሉ መተውና በእርሱ ፈንታ መልካም ማድረግን መማር/መለማመድ በየዕለቱ ሰራዬ ብሎ መያዝ ያስፈልጋል፡፡ ቀድሞ ያሳዩት የነበረ ያልተገባ ባህርይና ድርጊት አውልቆ በመጣል/በመተው መልካም ማድረግን በተግባር እያሳዩ ካልሆነ እውነተኛ የሆነ ንስሃ ግብቷል ማለት አያስችልም፡፡ ከልብ ያልሆነ መለወጥን በተግባር የማያሳይ ንስሃ ከእግዚአብሔር የሆነውን በረከት ከማግኘት ይከለክላል፡፡

ኢሳይያስ 1፡16-17፣ [16] ታጠቡ፤ ራሳችሁንም አንጹ፤ ክፉ ሥራችሁን ከፊቴ አርቁ፤ ክፉ ማድረጋችሁን ተዉ፤
[17] መልካም ማድረግን ተማሩ፤ ፍትሕን እሹ፣ የተገፉትን አጽናኑ፤ አባት ለሌላቸው ቁሙላቸው፤ ለመበለቶችም ተሟገቱ፡፡

ያዕቆብ 2፡19-20፣ አንድ እግዚአብሔር እንዳለ ታምናለህ፤ መልካም ነው፤ አጋንንትም ይህንኑ ያምናሉ፤ በፍርሀትም ይንቀጠቀጣሉ፡፡
[20] አንተ ከንቱ ሰው! እምነት ያለ ሥራ ዋጋ የሌለው መሆኑን ለማወቅ ማስረጃ ትፈልጋለህን?

2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡19-22፣ [19] ይሁን እንጂ፣ “ጌታ የእርሱ የሆኑትን ያውቃል፤” ደግሞም፣ “የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከክፋት ይራቅ” የሚል ማኅተም ያለበት የማይነቃነቅ የእግዚአብሔር መሠረት ቆሞአል፡፡ … [21] እንግዲህ ማንም ራሱን ከእነዚህ ከጠቀስኳቸው ነገሮች ቢያነጻ ለክቡር አገልግሎት የሚውል፣ የተቀደሰ፣ ለጌታው የሚጠቅም፣ ለመልካም ሥራም ሁሉ የተሰናዳ ዕቃ ይሆናል፡፡ [22] ከወጣትነት ክፉ ምኞት ሽሽ፤ በንጹሕ ልብ ጌታን ከሚጠሩት ጋርም ጽድቅን፣ እምነትን፣ ፍቅርንና ሰላምን ተከታተል፡፡ 1ዮሐ 2፡15-17፣ መዝ19፡163፣ 128፡፡

### ደጋግሞ ኃጢአት የሚያደርግ ይቅርታ ያገኛልን?

ማቴዎስ 18፡23…35፣ [23] “ስለዚህ መንግሥተ ሰማይ፣ በአገልጋዮቹ እጅ የነበረውን ሒሳብ ለመተሳሰብ የፈለገን ንጉሥ ትመስላለች፡፡ … [35] “ስለዚህ እያንዳንዳችሁ ወንድሞቻችሁን ከልባችሁ ይቅር ካላላችሁ፣ የሰማዩ አባቴም እንደዚሁ ያደርግባችኋል፡፡”

ማንኛውም ጌታ ኢየሱስን አምኖ የተቀበለ ሰው ሆን ብሎ ደጋግሞ ኃጢአት ማድረግ የለበትም፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ መልካም ፍሬ እያፈራ ማደግ ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን ደጋግሞ ኃጢአት የሚያደርግ አማኝ ስናይ፣ ይሄ ሰው እውነተኛ ንስሃ አልገባም የሚል ድምዳሜ መያዝ የለብንም፡፡ እኛም ለራሳችን

ባይታወቀንም በተመሳሳይ ሁኔታ ደጋግመን ኃጢአት እናደርግ ይሆናል። ከኃጢአት ጋር ለመዋጋት ግብግብ የያዝን ቢሆንም አሁንም ብዙ ያላስወገድነው ኃጢአት ይኖራል። እንደዚህ ብዙ ኃጢአት ያለብን መሆናችንን ከተረዳን እኛም ይቅር እንድንባል ከኃጢአት ጋር ውጊያችንን በመቀጠል እኛን ደጋግመው የሚበድሉንን ይቅር የማለት ግዴታ እንዳለብን ከፍ ብሎ የተገለጸው የእ/ር ቃል ያስረዳል። በሌላ በኩል ሁለት እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ (ኃጢአትን ወይም ጽድቅን ማድረግ) ፍላጎቶች በውስጣችን ስላሉ ያለማቋረጥ በተከታታይነት የምንመግበው አንዱ እየበረታና እያየለ እንደሚሄድ ማወቅ ያስፈልጋል።

እግዚአብሔር የልባችንን ፍላጎት ስለሚያውቅ በትጋታችን እየቀጠልን በፊቱ ድካመማችንና ኃጢአታችን መናዘዛችን በሕይወት ዘመናችን ሁሉ መቀጠል ይኖርብናል። እግዚአብሔርም ይወደዋል፣ ይረዳንማል።

ሉቃስ 13፡4-5፣ ወይም ደግሞ በሰሊሆም ግንብ ተንዶባቸው የሞቱት ዐሥራ ስምንት ሰዎች በኢየሩሳሌም ከሚኖሩት ሰዎች ሁሉ ይልቅ በደለኞች ስለ ነበሩ ይመስላችኋል? [5] አይደለም፤ እላችኋለሁ፤ ንስሓ ካልገባችሁ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ።"

2ኛ ጴጥ 3፥9፣ "አንዳንድ ሰዎች የዘገየ እንደሚመስላቸው ጌታ የተስፋ ቃሉን ለመፈጸም አይዘገይም፤ ነገር ግን ማንም እንዳይጠፋ ፈልጎ፣ ሁሉ ለንስሓ እንዲበቃ ስለ እናንተ ይታገሣል።"

©ኤልያስ ታሪኩ (ደ/ር) 2018 ዓ.ም.